የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ **08** አስ/ት/ፅ/ቤት ስር ለሚገኙ ት/ቤቶች የተዘጋጀ የ **6** ኛ ክፍል አካባቢ ሳይንስ ሞዴል ፈተና

I ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ

1. ወደ ህንድ ውቅያኖስ የማይገባው የምስራቅ አፍሪካ ወንዝ የቱ ነው;

   ሀ/ አዋሽ ለ/ ገናሌ ወንዝ ሐ/ ሩፋጅ ወንዝ መ/ ታና ወንዝ

2. በጥልቀቱ የመጀመሪያ ደረጃ ላይ ያለ የምስራቅ አፍሪካ ሀይቅ የቱ ነው;

   ሀ/ ቪክቶርያ ለ/ ጣና ሐ/ ታንጋኒካ መ/ ኤድዋርድ

3. የአስመራ ከተማ በዩኒስኮ የተመዘገበችበት ምክንያት የቱ ነው;

   ሀ/ የኢጣሊያን ቅኝ ግዛት ስር ስለነበረች

   ለ/ የበርካታ ህዝብ መኖሪያ ስለሆነች

   ሐ/ የምትገኝበት ከፍታ ከባህር ወለል በላይ 2000 ሜትር ስለሆነ

   መ/ የእድሜ ጠገብ ህንፃዎች ባለቤት ስለሆነች

4. የብዊንዲ ጥቅጥቅ ደን ብሔራዊ ፓርክ የት ሀገር ይገኛል;

   ሀ/ ዩጋንዳ ለ/ ቡርንዲ ሐ/ ታንዛኒያ መ/ ኬኒያ

5. ከምስራቅ አፍሪካ ሀገራት በህዝብ ብዛት የመጀመሪያ ደረጃ ያለችው ሀገር የቷ ናት;

   ሀ/ ኬኒያ ለ/ ኢትዮጵያ ሐ/ ታንዛኒያ መ/ ሞዛምቢክ

6. ከሚከተሉት ውስጥ የቁሳዊ ቅርስ ምሳሌ ያልሆነው የቱ ነው;

   ሀ/ ሀውልት ሐ/ የዳበረ የባህል ጀግንት

   ለ/ ገዳማት መ/ ቤተ መንግስት

7. ከሚከተሉት አንዱ የሕዝብ ባህርያት መገለጫ አይደለም

   ሀ/ የህዝብ ብዛት ሐ/ የህዝብ ስርጭት

   ለ/ የቴክኖሎጂ እድገት መ/ የሕዝብ እድገት ምጣኔ

8. የበረሃ እፅዋት የሆነው የቱ ነው;

   ሀ/ ወይራ ለ/ ዋርካ ሐ/ ቁልቋል መ/ ፅድ

9. በወርቅና ቆርቆሮ የምትታወቅዋ የምስራቅ አፍሪካ ሀገር የቷ ናት;

   ሀ/ ታንዛኒያ ለ/ ኢትዮጵያ ሐ/ ቡርንዲ መ/ ጅቡቲ

10. ዋነኛ የምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ምንድን ነው;

    ሀ/ ንግድ ለ/ ቱሪዝም ሐ/ ሳይንስና ቴክኖሎጂ መ/ ግብርና

11. ቅጠል አርጋፊ ደን ዛፎች ቅጠላቸውን የሚያረግፍበት ምክንያት የቱ ነው;

    ሀ/ በአካባቢው ከፍተኛ ዝናብ ስላለ ሐ/ የድርቅ ወቅትን ለማለፍ

    ለ/ የቅጠላቸው መጠን ትላልቅ ስለሆነ መ/ በአካባቢው ከፍተኛ ነፋስ ስላለ

12. በባህርና በውቅያኖስ መልክ የሚገኘው የውሃ ሀብት በመቶኛ ሲሰላ ምን ያህል ነው;

    ሀ/ 97% ለ/ 75% ሐ/ 1% መ/ 3%

13. ጥቁር አባይና ነጭ አባይ የሚገናኙት የት ሀገርና ከተማ ነው;

    ሀ/ ኬኒያ- ናይሮቢ ለ/ ኤርትራ-አስመራ ሐ/ ሱዳን-ካርቱም መ/ ግብፅ-ካይሮ

14. ሰው ሰራሽ የቱሪስ መስህብ የሆነው የቱ ነው;

ሀ/ የላሊበላ ውቅር አቢየተ ክርስቲያናት ሐ/ አዋሽ ብሔራዊ ፓርክ

ለ/ የታንጋኒካ ሀይቅ መ/ የኮሞሮስ ደሴት

15. በኬኒያ ለመጓጓዣነት እየዋለ ያለ ወንዝ የቱ ነው;

ሀ/ ታና ለ/ ገናሌ ሐ/ ሩቫማ መ/ ሩፋጂ

16. የታንዛኒያና የሞዛቢክ ድንበር በመሆን የሚያገለግለው የትኛው የምስራቅ አፍሪካ ወንዝ ነው;

ሀ/ የዛምቢዚ ወንዝ ለ/ የሩቫማ ወንዝ ሐ/ የሩፋጂ ወንዝ መ/ የዋቢሸበሌ ወንዝ

17. በሶማሊያ አሸዋ ሰምጦ የሚቀረው የምስራቅ አፍሪካ ወንዝ የቱ ነው;

ሀ/ የዋቢ ሸበሌ ወንዝ ለ/ የናይል ወንዝ ሐ/ የአዋሽ ወንዝ መ/ የገናሌ ወንዝ

18. ሰው ሰራሽ ሀይቅ የሆነው የቱ ነው;

ሀ/ ታንጋኒካ ለ/ ካሪባ ሐ/ ዝዋይ መ/ ኬቩ

19. ከሚከተሉት አንዱ ለአፈር መሸርሸር ምክንያት ነው;

ሀ/ ቁልቁል ማረስ ለ/ ጣምራ የደን እርሻ ሐ/ አግድም ማረስ መ/ ዛፎችን መትከል

20. በተንቀሳቃሽ ዱር እንስሳት የሚታወቀው የምስራቅ አፍሪካ ስነ ምህዳር የቱ ነው;

ሀ/ የደንከል በረሃ ሐ/ ማሳይ ማራ ፓርክ

ለ/ የብዊንዲ ጥቅጥቅ ደን ብሔራዊ ፓርክ መ/ የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ

21. የኢትዮጵያን ድንበር አቋርጦ የማይወጣው ወንዝ የቱ ነው;

ሀ/ ገናሌ ወንዝ ለ/ የአዋሽ ወንዝ ሐ/ የዋቢሸበሌ ወንዝ መ/ የአባይ ወንዝ

22. የእርሻና የከብት እርባታን ከደን ልማት ጋር ጎን ለጎን የሚያስኬድ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ዘዴ ምን ይባላል;

ሀ/ ዘር ማፈራረቅ ለ/ የእርከን ስራ ሐ/ ዳግም ድነና መ/ ጣምራ የደን እርሻ

23. በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ቁጥር የሚጨምርበት ወይም የሚቀንስበት ሁኔታን ማሳያ ምን ይባላል;

ሀ/ የህዝብ ስርጭት ሐ/ የዕታና የእድሜ ቅንብር

ለ/ የህዝብ እድገት ምጣኔ መ/ የህዝብ ብዛት

24. ቅጠለ ሰፋፊ ዛፎች የሚገኘው በየትኛው ከፍታ ነው;

ለ/ ከ 1000-2000 ሜትር ሐ/ ከ 1500-1800 ሜትር

ለ/ ከ 2000 ሜትር በላይ መ/ ከ 1000 ሜትር በታች

25. የዱር እንስሳ ያልሆነው የቱ ነው;

ሀ/ አቦሸማኔ ለ/ የዱር አህያ ሐ/ ግመል መ/ ግመሬ ዝንጀሮ

26. ዋና ዋና የምስራቅ አፍሪካ የእፅዋት አይነቶች በስንት ይመደባሉ;

ሀ/ በ 4 ለ/ በ 5 ሐ/ በ 3 መ/ በ 6

27. የበረሃ እፅዋቶች ባህርይ ያልሆነው የቱ ነው;

ሀ/ ሰፋፊ ቅጠል አለባቸው ሐ/ ረጃጅም ስር አላቸው

ለ/ እርሾህማ ግንድና ቅጠል አላቸው ሐ/ ወፍራም ቅጠል አላቸው

28. ዝርያቸው በመጥፋት ላይ ያሉ የብዊንዲ ጥቅጥቅ ደን ብሔራዊ ፓርክ የዱር እንስሳት ምን ይባላሉ;

ሀ/ ችምፓዚዎች ለ/ ዝሆኖች ሐ/ ድኩላ መ/ ጎሬዛዎች

29. በቅድመ ታሪክና በታሪክ ዘመን የሰው ልጅ የፈጠራና የስራ እንቅስቃሴ ውጤት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ የተፈጥሮ የለውጥ ሂደትን የሚያሳይ ሀብት ምን ይባላል;

ሀ/ ፈጠራ ሐ/ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ

ለ/ ቅርስ መ/ ፍልስፍና

30. የአክሱም ሀውልት በየትኛው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክልል ይገኛል;

ሀ/ በደቡብ ህዝቦች ለ/ በትግራይ ሐ/ በአማራ መ/ በአፋር

31. በምስራቅ አፍሪካ የሀይቆች አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ምክንያቶች መካከል ያልሆነው የቱ ነው;

ሀ/ የድርቅ መከሰትና የሀይቆች መጥፋት ሐ/ የሀይቆች በደለል መሞላት

ለ/ በአካባቢ ያለው የእፅዋት ሽፋን መቀነስ መ/ የተጠናከረ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ትግበራ

32. በኢትዮጵያ፣ ጅቡቲና በኤርትራ መካከል የሚገኝ ባለሶስት ጎን ስነ ምህዳር ምን ይባላል;

ሀ/ የደንከል በረሃ ሐ/ የአዌን ፏፏቴ

ለ/ የዩጋንዳ የተራራ ደን መ/ የሴሬንጌቲ ፓርክ

33. በአንድ በተወሰነ አካባቢና ወቅት የሚኖር ከልደት እስከ ሞት ባሉት ሂደቶች በሚያጋጥሙ መስተጋብር የሚያልፍ የሰው ልጆች ስብስብ ምን ይባላል;

ሀ/ ሀውልት ለ/ የህዝብ ብዛት ሐ/ ህዝብ መ/ ሀገር

34. የነጭ አባይ መነሻ የት ነው;

ሀ/ ጣና ሀይቅ ለ/ ቪክቶርያ ሐ/ የባሌ ተራሮች መ/ ኤቭ-ሀይቅ

35. ከምስራቅ አፍሪካ በኢንዱስትሪ የምትታወቀዋ ሀገር የቷ ናት;

ሀ/ ታንዛኒያ ለ/ ጅቡቲ ሐ/ ኬኒያ መ/ ኢትዮጵያ

36. ለተከታታይ ከአንድ አመት በማይበልጥ ጊዜ ለመዝናኛ፣ ለንግድ፣ ከመኖሪያ አካባቢ ውጭ ወዳሉ ቦታዎች የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ምን ይባላሉ;

ሀ/ ቱሪዝም ለ/ ሀገርን እወቅ ሐ/ ሆርቴከልቸር መ/ ፍልሰት

37. ርካሽ የመጓጓዣ ስልት በመባል የሚታወቀው የቱ ነው;

ሀ/ የአየር ትራንስፖርት ሐ/ የውሃ ትራንስፖርት

ለ/ የመንገድ ትራንስፖርት መ/ የባቡር ትራንስፖርት

38. የአዋሽ ወንዝ የሚነሳው ከየት አካባቢ ነው;

ሀ/ ከኦሮሚያ ምዕራብ ሸዋ ደንዲ ወረዳ ሐ/ ከደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ

ለ/ ከአርሲ ተራሮች መ/ ከሰሜን ኢትዮጵያ

39. የኢትዮጵያን ድንበር አቋርጦ ከወጣ በኃላ ጁባ በመባል የሚታወቀው ወንዝ የቱ ነው;

ሀ/ የአባይ ወንዝ ለ/ የባሮ ወንዝ ሐ/ የዋቢሸበሌ ወንዝ መ/ የገናሌ ወንዝ

40. ለተፈጥሮ ማዳበሪያ መስሪያ ለግበአትነት የማይውለው የቱ ነው;

ሀ/ ፕላስቲክ ለ/ የሞቱ እንስሳት ሐ/ የእንስሳት እዳሪ መ/ የእፅዋት ቅሪተ አካል